# ካይኔ በላይ?
(ክፍል አንድ)

ከዮሐንስ ታከለ

ሠራ አካላታቸው በጋለ ብረት እየተንጫጫና እየተንጨረጨረ፡የድርጅታቸዉንና የጓዶቻቸውን ገመና ላለማጋለጥ፣ እሳት ሊተፋ ያሞጠሞጠ ጠመንጃ ተደግኖባቸው “ሰፊው ሕዝብ ያቸንፋል!”ን እየፎከሩ የተሰዉ ጓዶቻችንን ለአፍታ ድቅን ይበሉባችሁ፡፡

ጥፍር ከጣታቸው፣ ፀጉር ከራሳቸው እስኪነጭ ድረስ በወፌ ላላ አካላታቸው እየተበላ፣ ህይወታቸው አልፎ ከነድንግልነታቸው እንዳልባሌ እቃ የትም የተጣሉ አዳጊና ወጣት የኢህአፓ ልጆች ኡኡታቸው እንቅልፍ ስለነሳኝ ነው ዛሬ ጉልድፍም ቢሆን ብዕር ያስነሳኝ።

በከፍተኛ 3 እስር ቤት በወርሃ ጥር 70 ዓ.ም. በሌሊት ሊገደሉ ከተወሰዱት 17 የኢሕአወሊ ለግላጋዎች፣ ሠንጋ ተራ መብራቱ ላይ፣ ላንጋኖ ጠጅ ቤት ፊት ለፊት ገድለው የጣሉት ጉልማ ይፈሩ የመጨረሻ እስትንፋሱ የቆመችው “ኢሕአፓ ፍቅር ነው!” ብሎ ነበር። ትክክል። ሠፊው የኢትዮጵያን ሕዝብ ከመውደድ የሰረጸ ፍቅር። ለተበደለ ከመቆርቆር የመነጨ ፍቅር! ፍቅርን ከግለፀልኝ ምሳሌ ላቅርብ፡፡ የፈጠራ ሳይሆን እውነተኛ ምሳሌ።

የዘጠኝ ዓመት ዕድሜ የነበረው ውልጃቦ ነስሬ አክስቱ ከገጠር አምጥተው ሊያኖሩት ወስነው አዲስ አበባ አመጡት። ከስልጢኛ ቋንቋ ሌላ የማያውቀው ውልጃቦ፣ ከልጅነቱ ጀምሮ እጅና እግሩን እየበላው የቆየውን ሙጀሌ በቀላሉ ባዝሊን እየቀቡለት ሁለት ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የእግሩ ንቃቃት ጠፍቶለት ለካ ያለስቃይ መኖር ይቻላል ከሚል በደስታ

ተሞላ። በሁለት በሦሥት ቀን ውስጥ አሳዛኝ ከሆነው የገጠር አኗኗሩ ተላቆ የጀመራት አዲስ ሕይወቱ ተድላ ሰጠችው።
የአክስቱ መኖሪያና ወጣት ማሕበራችን በትይዩ ይገኙ ስለነበር በጥዋት ተነስቶ ወደ ማሕበራችን እየመጣ ከዚያ ሁሉ ወጣትና አዳጊዎች ጋር በአጭር ቀናት በፍቅር ጭልጥ አለ። የነበረው ጓዳዊ ፍቅር ትዝ ይበላችሁ። ውልጃቦ ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለመኝታ ከወጣት ማሕበር እየተጠራ ነበር ወደቤቱ የሚሄደው። ሲነጋም እንደዚያው። የሁሉንም ኢሕአፓዎች ፍቅር ሲለገሰው፣ የሁሉም መዋደድና መፋቀር ውልጃቦ ውስጥ በአጭር ጊዜ ፍቅር ተከለበት። ትንሹ ውልጃቦ ከስልጢኛ በቀር ሌላ መግባቢያ ቋንቋ ባይናገርም በርካታ አማርኛና ስልጢኛ ቋንቋ የሚናገሩ ጓዶች በብዛት ያሉበት መንደር ስለሆነ ውልጃቦም በሚጣፍጥ ኮልታፋ አንደበቱ አማርኛን ከንግግር አልፎ የኢሕአፓንም መዝሙር ተካነበት። በቃ ኢሕአፓ ለውልጃቦ የፍቅር ኩሬ ሆኖ አግኝቶ ዋኘበት። አንዴ የውልጃቦ ወላጅ እናት ከገጠር መጥተው በነጋታው ቡና ተፈልቶ ቁርስ ሲቀርብ አክስት ያን ልጅ ጥሩልኝ ይሉና ከወጣት ማሕበር ተጠርቶ ለቁርስ ይሄዳል። ወላጅ እናት "ኮ ጭሎ መጭሃ" ይሉታል። መጣህ ወይ ማለታቸው ነው በስልጢ ቋንቋ። አክስት ቀበል ያደርጉና "እሮትን የሃፓ፣ ምሽትን የሃፓ፣ ኢነ ያፓ ምንግዝን ጭሎ?" ይሉታል አክስት። ጠዋትም ኢህአፓ ማታም ኢሕአፓ እያለ ይሮጣል። ለመሆኑ ኢሕአፓ ምንድን ነው?- ሲሉት እናቱ <u>"እሞ አቲንጉ ኢሕአፓ"</u> በማለት የእናቱንም የአክስቱንም አንገት እቅፍ አድርጎ ሳመው። ኢሕአፓ ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ መመለሻ ቃላት ያጣው ብላቴና እከኩን ያረገፉለትን አክስቱንና ወልዶ ያሳደጉትን እናቱን <u>እናንተ እኮ ናችሁ ኢህአፓ</u> በማለት ነበር የወላጆቹን ፍቅር ለኢሕአፓ፣ ኢሕአፓነትንም ለእናትነት መዓረግ ያበቃው። ይህ ለእኔ ትልቅ ትርጉም ሰጥቶ በሕይወቴ ያለፈ እውነት ነው።

አለማወቄ ደድሮብኝ በትንሽ ዓርፍተ ነገር ሊገለጽ የሚችልን የኢሕአፓን ፍቅር ለማሳየት ዝባዝንኬ አበዛህ

እንዳልባል ይቅርታ እጠይቃለሁ። ውልጃቦን የዛሬ 30 ዓመት በፍቅር ያነሆለለች ኢሕአፓ ሚሊዮኖችንም አስጥማለች። በነገራችን ላይ ያ አዳጊ ልጅ ፍሬን የበጠሰ መኪና በዚያው ወር 1970 ሕወቱን ቀጥፎታል፡፡ ዛሬ ቢኖር የ39 ዓመት ጎልማሳ ይሆን ነበር። ስለዚህ ከነፍቅሩ ተቀብሯልና ዓካሉ ቢፈርስም ዛሬም ከኛው ከህያዋኖቹ ጋር ይኖራል።

አንድዬ ልጆቻቸውን የተነጠቁ ወላጆች የኢሕአፓ ገድል ይነካቸዋል። ብቸኛ ልጃቸውን ያሬድን በነጣቂ የተነጠቁ እናት አስካለ ብቻቸዉን ማውራት ጀምረው ኖሮ ምነው ብቻዎን ያወራሉ ቢባሉ ነቃኋ! ነቃኋ ነው ያሉት። አዎ! ብዙ እናቶች በሃዘን ነቁ፤ ገሚሶቹ ታነቁ፣ ገሚሶቹ ተኮማተረው አለቁ በሃዘን። የእነዚህ ሽዎች የጋራ ቤት ነው ኢሕአፓ። ይቅርታ ይደረግልኝና የኢሕአፓ ኮርማ እኔ ነኝ ብሎ ሊፈጠም፣ ሊኖርም አይችልም፣ አይገባምም። ታዲያ ይሄንን ስል ኢሕአፓን ማጥፋት ማለት ወጣትን በጅምላ ፈጅቶ፣ ሬሳን መራመድ ነው ሲሉ የነበሩ አንጋችና አንጋቾችን እነሱንማ አይመለከትም። ራሱ ኢሕአፓ ውስጥ ታግለው አታግለው፣ የኢሕአፓ ኮርማ ካልተባልኩኝ ብለው፣ እኔ ያልኩት ካልሆነ በብዙሃን አልገዛም ብለው፣ ከጠላት ወግነው፣ ወጣቱን ያስፈጁትን የኢሕአፓ ታሪክ አይመለከታቸውም። ራሳቸው ጸንተው ዘልቀው አንቱ የተባሉ ታጋይ የኢሕአፓ አመራሮች ሆኑ ነባር አባላት ያደረጉት አስተዋጾየ ተጽፎ በቀይ ግምጃ ተጠቅልሎ ለመጭው ትውልድ በክብር ይተላለፋል እንጅ ከፓርቲው ሕገ ደንብ፣ ከፓርቲው ውስጠ ደንብ በላይ በማይክሮ ግራም ብልጫ የላቸውም። ወይም ለመብለጥ መሞከር ያካበቱትን ወርቅ ታሪክ ወደ ዛገ ብረት ይለውጥባቸዋልና።

አንዳንድ ግለሰቦች ሆኑ ስብስቦች የኢሕአፓን አፍ መሸበቢያ ወይም ያሸማቀቁ እየመሰላቸው የድርጅት ፍቅር ከሃገር በማስቀደም ክስ ኢሕአፓን ሲከሱት መደመጥ የተለመደ

ሆኗል። ግና ድርጅትስ የሚፈቀረው ሲኖር አይደለ? የሌለህን አታፍቅርም። ሆኖም በኢሕአፓ በኩል አባላቶቹ በፍቅር ሰንሰለት ተሳስረው፣ አንዱ ያንዱን ቁስል አጥቦ፣ አንዱ አንዱን ሽፍኖ ሕይወቱን የሰጠበት ክስተት ዝም ብሎ የተከሰተ ሳይሆን፣ ዓላማ ያሰረጸው ጓዳዊ፣ ድርጅታዊ ፍቅር እንጅ፣ ለሁሉም መሰረት የሆነው ሕዝባዊና ኢትዮጵያዊ ፍቅር እንጅ ከኛ በላይ የሚል አጉል ግብዝነት የወለደው አይደለም።

ታዲያ በአንዳንድ አባላት ሆነ መሪዎች ይህ ድርጅታዊ ትሥሥር ሃዲዱን ይስትና፣ ራሳቸው በፈጠሩት ምናባዊ ሚዛን ራሳቸውን ያስቀምጡና፣ ራሳቸዉን በራሳቸው ዕይታ ያሳብጡና፣ ባሳዛኝ ሁኔታ ራሳቸዉን ያፈነዳሉ። ራሳቸው ካካበቱት 36ኛ ሕዝባዊ የታሪክ ፎቅ ላይ፣ ለራሳቸው ሲሉ ይዘሉና ራሳቸውን ፈጣኑ ጅረት ውስጥ ይከታሉ። ሲፈራገጡም አጠገባቸው ካሉት አንድ ሁለቱን ይዘው በወራጁ ይበላሉ፣ በጣም የሚያሳዝን። በ1969-70 ገላችንን እንደልባችን ሰድደን ያመናቸው፣ የገዛ ጓዶቻችን ለወሬ ነጋሪ በማያስተርፍ መልኩ ከጠላት ጋር ሆነው ጨፈጨፉን፣ አስጨፈጨፉን። ያዛሬ 30 ዓመት አሳዛኝ ክስተት ዛሬም ድረስ ዓይናችንን ጨፈን ስናደርግ ወለል ብሎ የሚታየን የውስጥ አደጋ ጠባሳው ከህሊናችን ሳይጠፋ የጉርምስናው በጉርምስናው ዳግም ሊከሰት ቻለ። የያኔው ከዛሬው ልዩነቱ የዕድሜ ይሁን እንጅ ለም መሬት ቢያገኝ አደጋው መመሳሰሉ አይቀሬ ነበር፣ ኢንሻላህ የወደፊቱን። ታዲያ በሃሳብ መለየት፣ ተለያይቶ አናሳዎቹ ስም አውጥተው በራሳቸው ጎዳና ሽምጥ ቢጋልቡ ከልካይ እንደሌላቸው ሁሉ ከወጡ በኋላ ግን ስሙን መለጠፍ አይፈቀድላቸውም። ህዝብን ለማምታታትና ለማጭበርበር ካልሆነ በስተቀር!

ከላይ ይሄን ሁሉ በመዘርዘር ለትንሿ መደምደሚያየ ሃቅ ለማስጨበጥ የምሞክረው አቶ መርሻ ከእናት ድርጅታቸው በፍጹም አግባብነት በሌለው መንገድ፣ የሃሳብ ልዩነትን መሠረት በማድረግ ወይም እንደመነሻ በመጠቀም፣ ከተወሰኑ

ጥቂት ግለሰቦች ጋር ኮብልለው ካስኮበለሉ ከወርኃ ጥቅምት ወዲህ፣ ብዙ ያሉት ቢገርመኝም፣ ከአውስትራሊያው የኮሚኒቲ ራዲዮ (ቋጠሮ) ጋር ያደረጉት ቃለ ምልልስ በጣም ገርሞኛልም አሞኛልም። "አባላት ተስፋ ቆርጠው እንዳይበተኑ የተወሰደ እርምጃ" ሲሉ የተናገሩት የትኛውን ልዩ ጉባዔ እንደሆነ ተምታቶብኛል። በርግጥ የጥቅምቱ አብዮት ወይም ልዩ ጉባዔ ከሆነ (ነውም) አቶ መርሻን በጣም ሃሰት ነው ለማለት ይፈቀድልኝ። ምክንያቱም ሲያወሩ የሰማሁት ስለተረት ሳይሆን በዓይኔ ስላየሁት ሃቅ ነበርና። አቶ መርሻ አባላቱ ሳይሆን የተበተነው፣ ከንጋቱ 3 ሠዓት፣ ከአትላንታ ታማኝ ሾፌርዎ ጋር፣ ያችን የኢትዮጵያን ቁልፍ አንጠልጥለው በአራት በአራት መኪና ሲሄዱ አይቸዎት፣ እኔው ነኝ "አቶ መርሻ በጤና መታወክ ሳይሆን አይቀርም ወደ ሆስፒታል አቶ እከሌ የወሰዳቸው" ብዬ ከዕምነት የሰረጸ ስጋቴን ያወራሁት። ግን ዕምነቴን አልወነጀልበትም። ባይሆን ያፈርሰው! ኢሕአፓን የወለደ፣ ያሳደገ፣ የጎዳ፣ የጠቀመ እምነት ነዉና። ግን እርስዎ ዛሬ አባላትን ለማዳን የተወሰደ እርምጃ የሚለው አባባልዎ ከድርጊቱ የበለጠ በህመም ምክንያት የሚያስብልዎ ሃሰት ተናገሩ። ከአካሂያድ (ከፕሮሲጀር) ጋር ተያይዞ የነበረው አስልች ውይይት ዕልባት አግኝቶ፣ ወደ መፍትሂው የሚወስደው ሰርጽ ተዘርግቶ፣ ለ5 ሰዓታት ያህል በጥሞና እያዳመጥን አምሽተን፣ ጠዋት በአዲስ መንፈስ ተባብለን፣ ተቃቅፈን ከተለያየን በኋላ ምን አዲስ ሽይጣን መጣብዎ (የሃሳብ) በሌሊት ሂደው፣ ሲነጋ ጉባዔው ከተጀመረ በኋላ፣ የተወሰኑ ጥቂት ግለሰቦች ከኢሕአፓ ጋር መሥራት አንችልም ብለው፣ ፎክረው ኮቴዎን ተከትለው ሽምጥ የጋለቡት? እንደ ቃለ ምልልስዎ ሳይሆን፣ እርስዎ እንደአብሪ ሄዱ እንጅ እርስዎ የሰሯቸው ግለሰቦች ቀድመው አልጫኑም ወይም አልሄዱም። ያየሁትን ነው የማወራው።

ይቀጥላል ...